# ሠራዊትና ሠራዊቱ

በልጅግ ዓሊ

-፩-

<<ኢቲቪዮጵያ>>

ኢትዮጵያ በሁለት ትከፈላለች፣ የኢቲቪ ኢትዮጵያና የምንኖርባት ኢትዮጵያ። የኢቲቪ ኢትዮጵያ : ለም፣ የበለጸገች፣ ማርና ወተት የሚንዠቀዠቅባት፣ ዘይት ተርፎ የሚፈስባት፣ ስኳር የሚዛቅባት፣ ሆኖም ስግብግብ ነጋዴዎች የሚያስቸግሯት፣ ፍጹም ነፃ ምርጫ የሚካሄድባት፣ ዴሞክራሲ ያለልክ የሚፈስባት፣ ኮብልስቶን የሚያነጥፉ ሚሊየነሮች የሚፈልቁባት፣ አንድም ሰከንድ መብራት የማይቋረጥባት፣ ዜጎች በየእለቱ መንግሥታቸውን ለማመስገን ቃላት የሚያጡባት እና ፍጹም እንከን አልባ ስትሆን ሌላኛው የምንኖርባት ኢትዮጵያ ግን በአጭሩ እኛን ትመስላለች።ቃልኪዳን የሚባለው የአውራአምባ ታይምስ ጸሐፊ በአንድ ወቅት ይህችን ማርና ወተት የሚንዠቀዠቅባት የኢቲቪ ኢትዮጵያ ስም አወጣላት "ኢትቪዮጵያ"

ገጽ 74
ፒያሳ መሕሙድ ጋ ጠብቂኝ
መሐመድ ሰለማን

ዛሬ አውራምባ ታይምስ የለም። በወያኔ እንዲዘጋ ሆኗል። ዋናው የኢዲቶሪያል ማኔጀሩ ዳዊት ከበደ ሃገር ጥሎ ጠፍቷል። በተረጋጋ ሁኔታ በሰሜን አሜሪካ ስለሚገኘው ስለ ዳዊት ሁላችንም እየጮህን ነው። እንደ ቃልኪዳን ዓይነት የአውራምባ ጸሐፊዎች ምን እንደሆኑ የሚናገርም፣ የሚጮኽም አልሰማም። ሌሎቹ የአውራምባ ታይምስ ሠራተኞች ምን እንደ ደረሱ ብዙም የሚያስጨንቀን አይደለም። በአዲሱ በሥለጠነው ፖለቲካ መሪዎች ወይም ሃላፊዎች ሲታሰሩ ብቻ መጮኽ የተለመደ ነው። ከ1997 ምርጫ በኋላ የቅንጅት መሪዎች ይፈቱ! የሚለው መፈክር ይገርመኝ ነበር። ሌሎችስ ? ማንም የተናገረ የለም። የቅንጅት መሪዎች ከተፈቱ በኋላ አባሎቻችንን ይፈቱ ሲሉ አልተሰሙም። ትኩረት የተሰጠው የርስ በርሱ ፍትጊያ ላይ እንጂ ሌሎች በእስር ቤት የቀሩት ላይ አይደለም። መፈክርም አልነበረም። ወደፊትም የሚኖር አይመስለኝም። ራሳችንን ታዝበን መፈክራችንን ካልቀየርን ለተራው አባል፣ ለተራው ጋዜጠኛ፣ ለተራው ሕዝብ ማን ይታገልለት ይሆን? ለዛሬው እንደ አጋጣሚ አነሳሁት እንጂ የምጽፍበት ርዕስ አይደለም።

የኢትዮጵያ ቴሌቪዥንና ራዲዮ ወይም አዲስ ዘመን ጋዜጣ የሚስሏት ኢትዮጵያ ሌሎች ዓለም አቀፍ የመገናኛ ዘዴዎች ከሚስሏት ጋር ልዮነታቸው ትልቅ ነው። ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው ኤኮኖሚው አስራ አንድ በመቶ አድጓል ይሉናል። እነ ስተርን (የጀርመን መጽሔት) በሃገሪቷ በተለያየ ቦታ በርሃብ የሚያልቀውን ሕዝብ ያሳዩናል። ኢቲቪ የሃገሪቱ ታላላቅ ከተሞች አደጉ ይለናል። እነ ቢቢሲ ደግሞ ከቆሻሻ ቦታ እየለቃቀሙ የሚመገቡ ሕጻናትንና አዋቂዎችን ያስጎበኙናል። አዲስ አበባ የሚመላለሱ "የትራንስፎርሜሽን ኢንቨስተሮች" የቡና ቤቱን ውበት፣ የመዝናኛውን ቦታ ብዛትና በትንሽ ገንዘብ እንዴት መዝናናት እንደሚቻል ያወሩናል። ዘመድ አዝማድ ጋ ስንደውል ደግሞ የኑሮ ውድነትን ። ታዲያ ማንን እንመን?

ለብዙዎቻችን እንኳን ኤኮኖሚው ፕሮፖጋንዳውም አስራአንድ በመቶ አላደገም። እዛው ቀለበት መንገድ ላይ ነው የቆመው። ቀለበት መንገድና የአዲስ አበባ ፎቆች ለሚቀጥለው ስንት ዓመታት የወያኔ "ሃገሪቱ አድጋለች" የመነገጃ ፕሮፖጋንዳ እንደሚሆኑ አላውቅም። የሃገሪቱ እድገት አዲስ አበባ በተሰሩ ቡና ቤቶች ጥራት መጠን ለመለካት ጥረት የሚደርጉ ቅምጥል ሆዳሞች ከማንም በላይ ያናድዱኛል። አልፎ ተርፎ የሃገሪቱን የትምህርት እድገትና ጥረት እንግሊዘኛ እንጂ አማርኛ በማይችሉት ሕፃናት ብዛት ሊተምኑት የሚፈልጉ የዘመኑ ዲታዎች አጋጥመውኛል።

የሃገራችን ሰው ደሃ በሕልሙ ቅቤ ባይጠጣ . . . እንደሚለው አዲስ ዘመን ጋዜጣም ሆነ የኢትዮጵያ ራዲዮንና ቴሌቪዥን የመንግሥት ፕሮፖጋንዳ በተስፋ ይመግቡናል፣ በተስፋ ያኖሩናል ፣ በተስፋ ይገድሉናል። ገዦዎቻችችን ሃብታም የመሆን ተስፋ በልባችን እያሳደሩ እነርሱ የምድር ገነትን ሲኖሩ እኛ ደግሞ የምድር ገሃነም እሳት ውስጥ እንድንኖር ያደርጉናል።

በኦጋዴን በረሃ ስለሚገኘው ዘይት(ነዳጅ) ከሕፃንነታችን ጀምሮ እየሰማነው ኖርን። ዘይት ያላቸው ሃገሮች ሌላ ችግር የሌላቸው ይመስል አንዳንዶቻችን የችግራችን መቅረፊያ ዋናው በሃገራችን የዘይት መገኘት ነው ብለን ስንቋምጥ ከርመናል። በኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት አሜሪካኖች ዘይቱን ሊያወጡት ነው ብለው ወደፊት ከሚደርሳቸው ድርሻ የሚታሰብ ገንዘብ መበደር የጀመሩ ነበሩ ይባላል። ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ "የመንጌ" ነው። እናንተም እንደኔ አይታችሁ ታዝባችሁት ይሆን? አንድ ቀን በቴሌቪዥን ከቧንቧ በሚወጣ ፈሳሽ(የተፈጥሮ ጋዝ) ሲከፍትና ሲዘጋ። የቴሌቪዥን ዘጋቢው "ይህ አሁን የተገኘው ዘይት ከመውጣቱ በፊት የሚገኝ ነው" ብሎ ዘገበና ሳንበላ ጠግበን፣ ሳንጠጣ በደስታ ሰክረን ሰነበትን። አቤት ደስታችን። ቻዎ ድህነትና ረሃብ! ቻዎ ለቤንዚን መሰለፍ! ቻዎ ትምህርትና ጭንቀት!

ከአሁን ወዲያ አብዮታዊ ተሳትፎ ብቻ ነው ሃብታም የሚያደርገው ብለን በወጣት ማኅበር መሳተፍ የጀመርን ብዛታችን . . . በብዙዎቻችን ላይ ከፈገግታችን ብዛት ፊታችን ጥርስ ሆኖ ነበር ብል ማጋነን አይሆንም። ተፈጥሮን በቁጥጥር ሥር የምናውላት መስሎን ነበር። ለሚቀጥሉት ዓመታት መንጌ ያለ ተቃውሞ፣ እኛ ደግሞ በተስፋ መኖር ቀጠልን። የተጠበቀው ዘይት የውሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። መንጌን "ቆራጡን" ማንም የጠየቀው የለም። ግን ሁላችንም በተስፋ አብዮት ትንሽ አዘገምን።

መንጌ ሌላ ተስፋ መስጠት አሰበና ቅይጥ ኢኮኖሚ ብሎ አወጀ። ተጨፈረ።የደርግ ኤኮኖሚስቶችም ቅይጥ ኤኮኖሚውን ተስፋ ሰጭ ሲሉ አቆላመጡት። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቅይጥ ኢኮኖሚ የችግራችን መፍትሄ መሆኑን ዘገበ። ዜጎች የአየር በአየር ንግድ ኪሳቸውን ሲሞላው ማለም ጀመሩ። አንዳንድ የተሳካላቸው ነጋዴዎች ተግባር ተነገረ። ለመኮድ (ለመከላከያ ኮንስትራክሽን ድርጅት) የመጣውን እቃ ሰርቀው አየር ባየር ሸጠው የከበሩ እንደነበሩ ሲነገር ሁላችንም አየር ባየር ነግደን ሃብታም የመሆን ተስፋችን አበበ። አየር በአየር የተጀመረው ያኔ ሳይሆን ይቀራል?

በመንጌ ጊዜ ዘይት አስጨብጭቧል። በመለስ ጊዜ ደግሞ ሕዳሴ ግድብ። ስለ ሕዳሴ ግድብ የተወራው ስለ ድርቁ ከተወራው ጋር ሲመጣጠን የትየለሌ ነው። ሕዳሴ ግድብ መለስ የዓረቡ አብዮት ወደ ሃገራችን ይጋባል ብሎ በመፍራት ያመጣው አዲሱ የተስፋ ፕሮፖጋንዳ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ ካስጨበጨቡ መሪዎች መለስና መንጌ ይሆኑ ይሆናል። ይህንን ለታሪክ ተመራማሪዎች ልተው። እኔ ግን ብጠየቅ የመንጌ ንግግር ብዙ ያስጨበጭብ እንደነበር አስታውሳለሁ። አንድ ወዳጄ በኬንያ የኢትዮጵያ ኤምባሲ ውስጥ መንጌ በዛ ጎላ ባለው ድምፁ ያለውን ነግሮኝ ስስቅ ነበር።

"ጓዶች ችግራችን ባለ ብዙ ዘርፍ ነው ። ግን በቅርብ ቀን መፍትሄው ተግኝቷል። እንደ ሳዑዲ አረቢያም ሳይበዛ እንደ ጋቦን ሳያንስ መጠነኛ ዘይት በሃገራችንን ተግኝቷል ።"

ይህንን የሰሙ ምን እንደተሰማቸው አስቡት። የዛ ቀን ጭብጨባ ከሃገራችን ትልቁና ብዙ የቆየው ሊሆን ይችላል። እንደ መፈክሩ ለብዙ ደቂቃዎች ነው የቀጠለው ። መፈክሩ ትዝ ይላችኋል ። እናሸንፋለን! ፣ አንጥራጠርም! ፣ ሳይንሳዊ ሃቅ ነው . . . ሌላም ሌላም። መንጌ አለፍ አለፍ እያለ ሸንጎ ላይም እንደዚህ ያደርግ ነበር ።

በነገራችን ላይ መንጌ መጽሐፍ ጽፎ ለሽያጭ ሊያቀርብ ነው ተብሎ መነገር ከጀመረ ቢቆይም በቅርብ መጽሐፉ እንደሚታተም ማስታወቂያ አነበብኩ። "ትግላችን" ነው የሚለው። ፀሐይ አሳታሚ። እናንተም እንደኔ ይገርማችሁ ይሆን በሃገራችን ፖለቲከኛ ሲኮን ወዲያው ደራሲነት አብሮ ይሰጣል መሰለኝ። ማን እንደሚቀድም አላውቅም ፓለቲከኝነት ወይስ ደራሲነት ? ልደቱ (ክህደቱ) ሳይቀር ብዙዎቹ ፖለቲከኞች መጽሐፍ ጽፈዋል። መንጌ ይዞት የጠፋው ገንዘብ መነመነ መሰል አሁን ደግሞ በመጽሐፍ ሽያጭ ሊከብርብን ነው። እንደተለመደው ሟቹን ተስፋዬ ወልደሥላሴን ምሥክር ይጠራ ይሆን? መቼም ለውሸታም ሟች ነው ምስክሩ። ይህንን የደም ገንዘብ ለመብላት ያሰፈሰፉ አሳታሚዎችም ሆነ ለማንበብ የተቁነጠነጡ ይገርሙኛል። እውን የዚህን አረመኔ መጽሐፍ ገዝተን እንደገና ሃብታም ልናደርገው? እንዲህ ከሆነ በሕዝብ ደም የሚነግዱ ገዥዎቻችን ስለጡረታቸው ማሰብ የለባቸውም። "ሥልጣን ላይ በነበርኩበት ወቅት የሠራሁት ግፍ" ብለው መፃፍ ነው ። እኛ ደግሞ ለመግዛት እንኮለኮላለን ። የመንጌ ልጆች አይደለንም። ሰልፍ ያምርብናል። አሁን ደግሞ የመለስ ኢንቬስተሮች አይደለንም ሃገራችንንም ሸጠን ቢሆን ማትረፍ ነው።

መንጌ አሁን ደግሞ ምን የተስፋ እንጀራ እንደሚመግበን አላውቅም ። ግን በእሱ ፍቅር የተነደፉ በየቦታው መጽሐፉን ይዘው እንደሚዞሩ አልጠራጠርም። አፍቃሬ ሂትለር አሁንም ድረስ እንዳሉ ሁሉ አፍቃሬ መንጌም እንዲሁ ይኖራሉ። በየፓልቶኩም ለሕዝብ የሚያነቡ አይጠፉም። አንዳንዶቻችንም እንደተለመደው ቆመን እናጨበጭብ ይሆናል። መንጌ ራስ ወዳድነቱን ክዶ "መንጌ ሃገር ወዳድ" ነበር የሚለው ንድፈ ሃሳብ በውጭ ለተበተነው የኢሠፓ ሠራዊት በንድፈ ሃሳብ "ጓድ ሊቀመንበር" ያስታጥቁት ይሆናል። አጎቱ አሥራት ወልዴን ቀድሞ ከሞስኮ ወደ ዝምባዌ እንዳላከና ቦታውን እንዳላዘጋጀ " ተገደን ነው ሃገራችንን የለቀቅነው" ቢልም የሚገርም አይደለም። በደጋፊዎቹ ወሬው ቀድሞ ተበትኗልና። "እንኳን ሰው ዝንብም ገድዬ አላውቅ" . . . ሌላም ሌላም። ። ለሃገራቸው የተሰውትን እንደገና መግደል ከመንጌ መጽሐፍ የሚጠበቅ ነው። "የግንቦት ስምንቱን መፈንቅለ መንግሥት የሞከሩት የኢትዮጵያ ጠላቶች ስለሆኑ እኔ ሳላውቅ ተስፋዬ ወልደስላሴ እርምጃ ወስዶባቸዋል።" ሁሉንም ነገር በሞቱት የደርግ አባላት ለማሳበብ ይመስላል ሰውየው መፃሕፉን ያዘገየው።

መለስ ከመንጌ ይማራል። ለጡረታው ማሰብ አይገባውም ። ከመንግሥቱ የማይተናነስ ግፍ እየሠራ ነውና ለመጻሐፉ የሚጠቀምበት ትራጀዲም ይሁን ኮሜዲ የሚሆን ጥሩ ጥሬ ሃብት አጠራቅሟል። አሁኑኑ ለመጽሐፉ የሚሆኑ መረጃዎችን ሊያሸሽ ይገባል። የፎቶ መራጃዎች ደግሞ ጠቃሚነት አለው። በ1997 ዓ.ም. በጥይት ያስበረቀሰውን የወጣቶች ጭንቅላት እንደ መረጃ ቢያቀርብ መጽሐፉ ብዙ ገዥዎች ይኖሩታል። መለስ እንኳ ቢረሳው ቀዳማይ እመቤታችን በገንዘብ ቀልድ አታውቅምና መረጃውን ሰብስባ ታስቀምጣለች።

መንግሥቱ መጽሐፉን ለማሳተም ተስፋዬ ወልደ ሥላሴ እስከሚሞት እንደጠበቀው መለስ መጠበቅ የለበትም። የተስፋዬ ወልደ ሥላሴን መጣኝ ክንፈን ቀድሞ ስለገደለ ወይም ስላስገደለ አሁን በሰፊው መዋሸት ይችላል። "እንኳን ሰው ዝንብ አልገደልኩም ፣ አላስገደልኩም ፣ ከደግነቴ ብዛት ስሞት መንግሥተ ሰማየትም ቢሆን ስልጣን አላጣም"ብሎ ሊጽፍ ይችላል ። ማን ተናግሮት ! እኛም እንሰለፋለን፣ እንገዛለን ። የትራንስፎርሜሽን ኢንቬስተሮች አይደለንም። መለስ ጽፎ እኛ እንዴት ሳንገዛ እንቀራለን።

መለስ መጽሐፍ ለመጻፍ ቅድመ ዝግጅቱን ጨርሷል። ቢያንስ ቢያንስ ከሆዳም የኪነጥበብ ሰዎች የወርቅ ብዕር ለኪነጥበብ ላደረገው አስተዋፅዖ ተሸልሟል። የሠራዊት ፍቅሬና ሠራዊቱ የወርቅ ብዕር ሸልመውት የለ። እነ ሠራዊት ፍቅሬ ለመለስ ሽልማቱን ሲሰጡ ለኪነ ጥበብ እድገት ላደረገው አስተዋጽዖ ነው ብለው ሲያስቁኝ ነበር። ከቴም (ድንቄም) ኪነጥበብ! እንዲህ ቢሉት ይሻል ነበር ፡ -

"በሃገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን ታዋቂና ጋዜጠኞች ፣ የኪነት ሰዎች ፣ እና ደራሲያንን ባያባርሩልን ኖሮ እኛ ባለን ችሎታና ዕውቀት አሁን የደረሰንበት አንደርስም ነበር። ለዚህ ላደረጉልን ውለታ ይህንን የወርቅ ብዕር ሸልመንዎታል። በዚያ እየፃፉ መመሪያ ይስጡን። እኛም እንፈጽማለን።"

ይህንን ቢሉ ለትንሿም ሐቅ ቢሆን እናጨበጭብላቸው ነበር። የብዕሩ ምሥጢር ትንሽ ቆይቶ ነው የተጋለጠው። ሠራዊት ከነሠራዊቱ ባለፈው እንቁጣጣሽ ዓባይ ዓባይ ቢሉ በምን ብዕር እንደተፃፈ አይገባንም ማለት ነው? አይ ሠራዊት ፍቅሬና ሠራዊቱ ።

ተስፋ መመገብ የሚችሉ መሪዎቻችን ሥልጣን ላይ ሳሉ በተስፋ፣ ከስልጣን ሲወገዱ ደግሞ ለእነርሱ ኮሜዲ በሆነውና የእኛን ትራጄዲ ባቀፈው መጽሐፍታቸው ያስደስቱናል። እኛ ደግሞ ቀደም ተርበን፣ ታርዘን ስናገለግላቸው እንዳልከረምን አሁን ደግሞ እንዳይከፋቸው በኢኮኖሚ ልንደግፋቸው ነው። ምን ዓይነት ሕዝብ ነን? የኛኑ ስቃይ በአሰቃዮቻችን ሲተረክ ከፍለን የምንገዛ።

በአሜሪካ ሃገር ስንት የሕግ ሊቃውንት የሆኑ ኢትዮጵያውያን አሉ። ለመሆኑ ይህ አረመኔ ከሚያገኘው ገንዘብ ልጆቻቸው ለተገደሉባቸውና፣ ጧሪ ላጡ አሮጊቶችና ሽማግሌዎች ካሣ መጠየቅ የሚቻልበት መንገድ አይኖርም? ይህ አረመኔ እነዚህን ሽማግሌና አሮጊቶች ጧሪ የነበሩ ልጆቻቸውን ገድሎ፣ ያለ ጡረታ አስቀምጦ፣ ኢትዮጵያን ለእርጉም ዘረኛ አሳልፎ ሠጥቶ አሁን እሱ ተዝናንቶ በመጽሐፍ ሽያጭ ሊከብር አይገባም። የኢትዮጵያ ጠላት እስካልሆነ በቀር "ሀገራችሁ መቼም ልትተካቸው የማትችለውን ዜጎቿን አጥፍቼ ለተኩላ የተውኩላችሁ ኢትዮጵያችሁ ይህንን ትመስል ነበር" የሚለውን ጽሁፉን ለማንበብ ጉጉት ሊኖረው የሚችል ኢትዮጵያዊ መኖር የለበትም፡፡

እኔ እንኳን በማውቀው በቅርብ ኦ. ጄ ሲምሰን የሚባለው ጥቁር አሜሪካዊ የቀድሞ ሚስቱንና ጓደኛዋን ገድሏል ተብሎ ከተከሰሰ በኋላ ምንም እንኳን ነፃ ቢለቀቅም ስለ ሁኔታው መጽሐፍ ለመፃፍ ፈልጎ ሁሉም አሳታሚዎች በሚኞቹ ደም አታተርፍም በማለት አናሳትምም በማለታቸው ሳይታተም ቀርቷል። ይህንን ጉድ ፀሐይ አሳታሚ አልሰማም ማለት ይሆን? የደም ገንዘብ ነውና ተጽፎ ይቀመጣል።

መለስ እንደ መንግሥቱ መጽሐፍ ጽፎ ከሥልጠን በኋላ አለ ሃሳብ እኖራለሁ ብሎ ካሰበ ደግሞ ሁሉም አምባገነኖች እንደ መንግሥቱ አልተሳካላቸውም። እንደ ሳዳም ፣ እንደ ጋዳፊም ዓይነት እድል እንዳለ ማሰብ ያስፈልጋል። የሳዳምም ፣ የጋዳፊም ደጋፊዎቻቸው ምን እንደደረሰባቸው ማጤን ደግሞ ለወያኔ ሠራዊቶች ጥሩ ነው። ለነገሩ ቀዳማዊት እመቤቱ ጉድ ካላደረገችው በስተቀር እሱ ከሠሞነኛው አብዮት ጥቂት ሳይማር ይቀራል? ያለበለዚያ መጽሃፍ እንኳ መሸጥ አይቻልማ !

የመንግሥቱን መጽሐፍ አሁን የምንገዛ ነገ የመለስንም መጽሐፍ ከመግዛት አንቆጠብም። ገዥዎቻችን ከስልጣን ሲባረሩም ሃብታም አድርገን ልናኖራቸው አይገባም። ሁላችንም መጽሐፉን ባለመግዛት ተቃውሟችንን ልናሳይ ይገባል። ይህንን ካደረግን ብቻ ነው በአምባገነኖቹ የተገደሉትን ሰማዕታት ልንታደጋቸው የምንችለው።

ለማንኛውም በተስፋ ያደግን ነንና በተስፋ እንኖራለን።
በተስፋ የሚኖሩ ሁሉ በሰላም ይክረሙ ።

Beljig.ali@gmail.com
በልጅግ ዓሊ
ሎንዶን፣ ትዕሳስ 2011